የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት
ALL ETHIOPIA UNITY PARTY

☎ +251-111 55 35 06, +251-111 55 17 89, +251-116-55 12 56 Fax. +251-111 55 31 55
17013 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ Addis Abeba Ethiopia, Website:- www.kaeup.org e-mail: ... ethionet.et

ቁጥር
Ref. No. ________
ቀን
Date ________

# መኢአድን ከውጭና ከውስጥ ጥቃት በመጠበቅ ትግላችንን ለማፋጠንና ለማጐልበት ቆርጠን ተነስተናል!

## ከመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት /መኢአድ/ የተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት /መኢአድ/ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ለመልካም አስተዳደር መስፈን፣ ለህግ የበላይነት መኖር፣ ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ እና ለሰብአዊና ለዲሞክራሲያዊ መብቶች መከበር በመታገል ላይ የሚገኝ አንጋፋ ድርጅት ነው።

ይህን የተቀደሰ ዓላማውን ለማሳካትና የኢትዮጵያን ህዝብ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች ለማስወገድ በሚያደርገው ብርቱ ጥረት ቀላል የማይባሉ የውጭና የውስጥ ፈተናዎች ሲገጥሙት ቆይተዋል። ፈተናዎቹ የጉዞውን አቅጣጫ አላስቀየሩትም፤ የቆራጥ አመራሮቹና አባሎቹ ከፍተኛ ትግል ፈተናዎቹን እየተወጣ የተነሳለትን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ይበልጥ እንዲጓዝ አስቻሉት እንጂ።

ባለፉት ዓመታት ገዥው ፓርቲ በድርጅታችን ላይ ሲያደርስ የቆየው ጥቃት አልበቃ ብሎት አሁንም በየዞኑ ባሉ የፓርቲያችን አመራሮችና አባሎቻችን ላይ እያደረሰ ያለው መከራና እንግልት ተጠናክሮ ቀጥሏል። ገዥው ፓርቲ የዚህ ዓይነቱን የውጭ ጥቃት ከመፈጸሙም በተጨማሪ በሰርጐ ገብ መልዕክተኞቹ አማካኝነት ድርጅታችንን ለማፍረስ የሚያደርገው እንቅስቃሴ መልኩን የለወጠ የጥቃቱ ስትራቴጂ ሆኖ ይታያል።

መኢአድ የታህሳስ ወር 2003 ዓ.ም ጠቅላላ ጉባዔውን ሲያከናውን እኩይ ዓላማ ያላቸው የውስጥ ኃይሎቹ የውጭ ኃይሎች የአፍራሽነት መልዕክተኛ በመሆን ጉባዔውን ለማወክ ያደረጉት ጥረት ሳይሳካ ቀርቷል። በአቶ ማሙሸት አማረ የሚመራው የአፍራሽ ቡድኑ አባላት ከጠቅላላ ጉባዔው በኋላም የተሰጣቸውን የቤት ሥራ በመቀጠል በአመራሩ ላይ ችግር ሲፈጥሩ ቆይተዋል። ለምሳሌም ያህል፦ በሌለ ሥልጣናቸው ከፍተኛ አመራሮችን አግደናል ብለው መግለጫ ሰጥተዋል። ለጥቂት ቀናት ጽ/ቤታችንን በመቆጣጠር ማህተምና ሌሎች ጠቃሚ ሰነዶችን ከልክለዋል። የሃሰት ፕሮፖጋንዳ ነዝተዋል። ነገር ግን የፓርቲው

አመራርና አባላት አንድ በመሆን በህጋዊ መንገድ እንቅስቃሴያቸውን በማክሸፍ ጽ/ቤታችንን ተረክበናል፡፡

የመኢአድ ማዕከላዊ ም/ቤት በፓርቲው ውስጥ የተፈጠረውን ችግር በመመርመር የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥ ለሐምሌ 30 ቀን 2003 ዓ.ም በመጠራቱ ሐምሌ 28 እና 29 ቀን 2003 ዓ.ም የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው አስፈላጊ መሰናዶ ለማድረግ በጽ/ቤቱ ውስጥ ስብሰባዎችን አካሂዷል፡፡ ሐምሌ 29 የፓርቲውን የ7 ወር ሪፖርትና የሐምሌ 30 ቀን 2003 ዓ.ም የማዕከላዊ ም/ቤት አጀንዳዎችን እየተወያየ በማጽደቅ ላይ እንዳለ በአቶ ማሙሸት አማረ የሚመራው የአፍራሽ ቡድን ጽ/ቤቱን ያወክ ጀመር፡፡ ለዚህ የማወክ ተግባር ደግሞ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአራዳ ምድብ ችሎትና የአራዳ ክ/ከተማ ወረዳ ፖሊስ መምሪያ ከፍተኛ እገዛ ታክሎበታል፡፡ ይኸውም፦ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቱ ለአራዳ ክ/ከተማ ወረዳ 1 አስተዳደር ጽ/ቤትና ለአራዳ ክ/ከተማ ፖሊስ መምሪያ በሰጠው ትዕዛዝ ‹‹ከሳሽና ተከሳሽ በተገኙበት ታሽገው የቆዩትን የድርጅቱን መዝገብ ክፍል፣ ሒሳብ ክፍልና ንብረት ክፍል የተዘጋውን በር በጥንቃቄ ገንጥላችሁ በመግባት እንድትፈጽሙ›› በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ይህንን ትዕዛዝ መሠረት በማድረግም በምክትል ኢንስፔክተር ገብረአሊፍ ታረቀኝ መሪነት የአራዳ ክ/ከተማ ፖሊስ መምሪያና የአራዳ ክ/ከተማ ወረዳ 1 አስተዳደር ሕጋዊ ውክልና ለሌላቸው ኃይሎች ጽ/ቤታችንን ለማስረከብ ያደረጉት ሙከራ የገዥው ፓርቲ ከኋላ ሆኖ የሚያደርገውን እንቅስቃሴ በግልጽ ያሳየበት አሰራር ነበር፡፡

ጽ/ቤቱን ሰብረው የገቡ የፖሊስ ኃይሎችንና የገዥው ፓርቲ የውስጥ አርበኞችን የመኢአድ የአዲስ አበባና የየክፍለ ከተሞች አመራርና አባላት ትዕግስት በተሞላበት ሰላማዊ ሁኔታ ጽ/ቤቱን ላለማስያዝ የከፈሉት መስዋዕትነት በፓርቲያችን የትግል ታሪክ ውስጥ ጉልህ ሥፍራ ይይዛል፡፡

በዚህም ወቅት የአፍራሹ ኃይል በአባሎቻችንና በአመራሩ ላይ የተለያዩ ጉዳቶች አድርሷል፡፡ አሲድ በመድፋት ክቡር የሆነውን የሰው ልጅ አካል አቃጥለዋል፡፡ ጭንቅላት ፈንክተዋል፡፡ አንገት አንቀዋል፡፡ እግር ሰብረዋል፡፡ በተለያዩ የሰውነት ክፍሎች ላይ ድብደባ ፈጽመዋል፡፡ ድንጋይ በመወርወር የግቢውን ድንኳ ቀዳደዋል፡፡ አስነዋሪ የስድብ ውርጅብኝ አውርደዋል፡፡ ህግ ሊያስከብር ይገባ የነበረው የፖሊስ ኃይልም ጋጠ ወጥ እንቅስቃሴያቸውን በዝምታ ተመልክቷል፡፡ ድርጊቶቻቸው ምን ያህል ህገ-ወጥነታቸውን ከማረጋገጡም በላይ የግለሰቦቹን ማንነት ቁልጭ አድርጐ አሳይቷል፡፡

የአራዳ ምድብ ፖሊስ መምሪያም ቁጥራቸው 46 የሆነ የፓርቲውን አባላትና አመራሮችን ወደ ፖሊስ ጣቢያ በመውሰድ ለተወሰኑ ሰዓታት በማቆየት ያለፍቃዳቸው

ፎቶግራፍ በማንሳትና ቪዲዮ በመቅረጽ ህግ ከማስከበር ይልቅ ህገወጥ ተግባር ፈጽሟል፡፡ አሳዛኙ ድርጊት በመኢአድ ጽ/ቤት በተፈጸመበት ወቅት የፖሊስ አባላት ሁኔታውን ለመዘገብ የመጡ የግል ጋዜጠኞችን መረጃ እንዳይሰበስቡ የፕሬስ አዋጁ የሰጣቸውን መብት በመግፈፍ አዋክበዋቸዋል፡፡ ይህም በፓርቲው ላይ ከተሰነዘሩት ጥቃቶች አንዱ አካል ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ሙከራው ከአሁን በፊት በሌሎች አንዳንድ ፓርቲዎች ላይ የተፈፀመውን ህገወጥ ተግባር በመኢአድም ላይ ለመድገምና ህጋዊ የፖርቲውን አመራር ከጽ/ቤት አስወጥቶ ህገወጡን ቡድን በመኢአድ አመራርነት ዕውቅና ለመስጠት የተቀጣ ድርጊት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

የመኢአድ ተወካዮች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአራዳ ምድብ ችሎት የሰጠውን ትዕዛዝ ለማስቆም አስቸኳይ እርምጃ በመውሰድ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ፍትሃ ብሔር ምድብ ችሎት አቤት ብለዋል፡፡ በዚሁ መሠረትም ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ለአራዳ ምድብ ችሎት የእግድ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

በተጨማሪ እነዚህ የአፍራሽ ቡድን አባላት በፈፀሙት የድሲኘሊን ጥሰት በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ፓርቲው ለህግና ሥነ-ሥርዓት ኮሚቴ ያቀረበውን የዲስኘሊን ክስ ቀርበው ምላሽ ከመስጠት ይልቅ የፓርቲውን ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴና የህግና ሥነ-ሥርዓት ኮሚቴ እንደማያምኑበትና እንደማይቀበሉት ገልጸዋል፡፡ ከፓርቲው ተሰናብተው ባሉበት ሁኔታ የማዕከላዊ ም/ቤት ስብሰባ ለመጥራት የራሳቸውን ኮሚቴ አቋቁመው መንቀሳቀሳቸው የህገወጥነት ትልቁ መገለጫቸው ሆኖ ታይቷል፡፡

ሐምሌ 30 ቀን 2003 ዓ.ም በየኢየሩሳሌም ሆቴል በመኢአድ የተጠራውን የማዕከላዊ ም/ቤት ስብሰባ ለማደናቀፍ ይኸው የአፍራሽ ቡድን አባላት ከተለያዩ ክልሎች ለጉባዔው በመጡ የማዕከላዊ ምክር ቤት አባላት ላይ ከሰላማዊ ትግል በተቃረነ መልኩ በህገ ወጥ መንገድ ጫና ሲፈጥሩ ቆይተዋል፡፡ ይኸውም ጉባዔተኛው ወደስብሰባው አዳራሽ እንዳይገባ ሁከት ከመፍጠር ጀምሮ የፓርቲውን ኘሬዝዳንት መኪና እስከ መስበር ድረስ የመጨረሻ የተስፋ ቆራጭነት ሙከራቸውን አድርገዋል፡፡ ነገር ግን በማዕከላዊ ምክር ቤቱ አባላት ትግል ጉባዔው እንደታቀደው ለመካሄድ ችሏል፡፡

ዛሬ በመኢአድ ላይ ክንዳቸውን የሰነዘሩት የአፍራሹ ቡድን አባላት ለረጂም ዓመታት በፓርቲያችን አመራርነት በነበሩበት ወቅት ከአባላትና ከህዝብ የሚገኘውን የፓርቲ ገንዘብ የገቢ ምንጫቸው በማድረግ ሲተዳደሩበት ቆይተዋል፡፡ ከነበሩበት ኃላፊነት መነሳታቸው ደግሞ የለመዱትን ገቢ ለማገኘት የማያስችላቸው በመሆኑ በኃይል በመጠቀምና የገኘው ፓርቲም

መሣሪያ በመሆን ተልዕኮአቸውን ለመፈፀም የፖሊስ ኃይልን አጋዥነት መጠቀማቸው የመጨረሻ አማራጫቸው ሆኖ ታይቷል፡፡

በሌላም በኩል በውጭ ሃገር በሚገኙ የመኢአድ ድጋፍ ሰጭ ድርጅቶች ውስጥ ፓርቲያችንን ለማፍረስ የሚያንቀሳቅሱ ጥቂት ግለሰቦች ሰርገው በመግባት ለፓርቲው ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ከአባላትና ከደጋፊ የሚሰበሰበውን ገንዘብ ስህገወጡ ቡድን በመላክ መኢአድን ለማወክ ተጠቅመውበታል፡፡ ይባስ ብለው ፓርቲው ህገ ደንቡን ተጠቅሞ የማዕከላዊ ምክር ቤት ስብሰባን ለመጥራት እየተዘጋጀ ባለበት ወቅት የማዕከላዊ ም/ቤቱን አጠራር አስመልክቶ በፓርቲው ላይ ጫና በመፍጠር ከደንብ ውጭ ጥሪ እንዲደረግ ሙከራ አድርገዋል፡፡ ይህ አድራጎታቸው በፓርቲያችን ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያ ቢሆንም ለዚህ እኩይ ተግባር ያገኙት ምላሽ ግን የማያዳግም ነበር፡፡

በተለያዩ ጊዜያት በፓርቲያችን ላይ የውስጥና የውጭ ኃይላት ችግሮች በፈጠሩብን ጊዜ ሁሉ ከጎናችን በመቆም አስፈላጊውን ማበረታቻ ላደረጋችሁልን የድጋፍ ሰጭ ድርጅቶች በሙሉ ልባዊ ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡

የማዕከላዊ ምክር ቤት ጉባዔ ከብዙ ፈተናዎች በኋላ በተያዘለት ዕቅድ መከናወኑ ለድርጅቱ ስኬት ሆኖ ይቆጠራል፡፡ በጉባዔውም ላይ የፓርቲው ዓበይት ክንውኖች፣ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ ሀሳቦች እንዲሁም

የፓርቲው የወደፊት ዕቅዶች ውይይት ተካሂዶባቸዋል፡፡ ጉባዔው የተለያዩ ውሳኔዎችን አስተላልፏል፡፡ ከውሳኔዎቹ ውስጥም የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡

1. በአቶ ማሙሸት አማረ አስተባባሪነት እየተንቀሳቀሱ ባሉት የአፍራሽ ቡድን አባላት ላይ የህግና ሥነ-ሥርዓት ኮሚቴ የወሰደውን የጥፋተኝነት ውሳኔ እና የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ያፀደቀውን የማዕከላዊ ኮሚቴ በሰማንያ (80) ድምጽ ድጋፍና በሁለት (2) ተቃውሞ በማሳለፍ ከአመራርነትና ከፓርቲ አባልነት እንዲሰናበቱ ወስኗል፡፡

2. በተጓደሉ የም/ቤት አባላትና በተሰናበቱ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ምትክ የሟሟያ ምርጫ አከናውኗል፡፡ በዚሁ መሠረትም፡-

| | |
|---|---|
| 2.1 ተቀዳሚ ምክትል ፕሬዝዳንት | አቶ ወንድምአገኝ ደነቀው |
| 2.2 ምክትል ፕሬዝዳንት | አቶ አሰፋ ሀብተወልድ |
| 2.3 ዋና ጸሀፊ | አቶ ተስፋዬ ታሪኩ |
| 2.4 የውጭ ጉዳይ ኃላፊ | ዶ/ር በዛብህ ደምሴ |

2.5 የድርጅት ጉዳይ ኃላፊ — አቶ ማህተመ በኩረ

2.6 የደቡብ ቀጣና አስተባባሪ — አቶ እንድሪያስ ኤሮ

2.7 የሰሜን ቀጣና አስተባባሪ — አቶ በለጠ ገብሬ

2.8 የምዕራብ ቀጣና አስተባባሪ — አቶ ብርሃኑ ወልደሰንበት

2.9 የመሥራቅ ቀጣና አስተባባሪ — ሻ/ም ግዛው ተሰማ

2.10 የማዕከላዊ ቀጣና አስተባባሪ — አቶ ብዙአየን ገብረማርያም

2.11 የሕግና ሥነ-ሥርዓት ኃላፊ — አቶ ፀጋዬ ግዛው

2.12 የምርጫ ጉዳዮች ኃላፊ — አቶ ገለቱ ጀጀርሳ

2.13 የአስተዳደርና ፋይናንስ ኃላፊ — አቶ አዳሙ ተሰማ

2.14 የሴቶች ጉዳይ ኃላፊ — ወ/ሮ ዕፀገነት ይልማ

2.15 የወጣቶች ጉዳይ ኃላፊ — አቶ አቤል ሙሴ እና ሌሎችም የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላትን መርጧል።

ማዕከላዊ ምክር ቤት አቶ ያዕቆብ ልኬንም ከተቀዳሚ ምክትል ፕሬዝዳንትነትና ከሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባልነት እንዲሰናበቱ አድርጓል።

በመጨረሻም የመኢአድ የማዕከላዊ ምክር ቤት በወቅታዊ ጉዳዮች ላይና በፓርቲው አጠቃላይ የወደፊት የትግል አቅጣጫዎች ላይ በመነጋገር ባለ 9 ነጥብ የአቋም መግለጫ በማውጣት ውሳኔዎችን አስተላልፏል።

*አንዷት ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!!*

**የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት /መኢአድ/**

**ነሐሴ 12 ቀን 2003 ዓ.ም**

**<u>አዲስ አበባ</u>**